**የከተማ-ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የጋራ ተቆማት ማስተር ፕላን**
ቨርችዋል የማህበረሰብ ተሳትፎ
የቪዲዬ ፅሁፍ መግለጫ (ትራንስክሪፕት)

**ገፅ (ስላይድ) 1፣**

ባለፈው ዓመት የአሌክሳንደሪያ ከተማ እና አሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች (ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ.) የወደፊቱን የሚያሳይ የትብብር ስራ የጋራ የሆነ የከተማው እና የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተቋማት ዋና ማስተር ፕላን(JFMP) አብረው ሲያዘጋጁ ነበር።

ዛሬ ስለዚያ ሂደት ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ለማድረግ የ12 ደቂቃ ቪዲዬ እናቀርባለን። ከዚያም ያለዎትን ሃሳብ አስተያየት በአጭር መጠይቅ እንዲገልፁ እንጠይቃለን።

**ገፅ (ስላይድ) 2፣**

እስከ አሁን የተፈጠረውን ሁኔታ እና አሁን ያለንበትን የሂደት ደረጃ እንገልፃለን ። ከዚያም ቀጣዩ ሂደት ምን እንደሚሆን በማውራት የእናንተን አስተያየትና ሃሳብ እንጠይቃለን።

የቪዲዬ መጨረሻ የሚያካትተው መረጃ መጠይቁን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ ቪዲዬውን ሲፈልጉ በመሃል ማቆም ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የፕሮጀክቱን ድረገፅ ይመለከቱ ።

**ገፅ (ስላይድ) 3፣**

በመጀመሪያ እስከአሁን ምን እንደተከናወነ እናውራ።

በመላው ከተማ ውስጥ በርካታ ተቆማት እና አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ እናውቃለን - አሮጌ ህንፃዋችን ዘመናዊ እና ጥገና ማድረግ ከማስፈለጉም በላይ አዳዲስ ተቆማትና እንደ እሳት መከላከያ እና ትምህርት ቤቶችም መጨመር ይኖርብናል።

ሆኖም ያለን አቅም ውስን ነው። የኮሚዪኒቲውን ፍላጎት በሙሉ ለማሟላት መፍትሄ ለማግኘት ፈጠራ የታከለበት እቅድ ያስፈልገናል።

**ገፅ (ስላይድ) 4፣**

የጋራ ተቆም ማስተር ፕላን ሶስት ቁልፍ ነገሮች ይይዛል፤ የፕሮጀክት ውሳኔዋችን ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዋች ውስጥ ማስተላለፍ የሚያስችል ማእቀፍ ማዘጋጀት፣ በመላ ከተማው ያሉ ፍላጎቶችን በመገምገም መሰረታዊ መረጃ ማሰባሰብ፣ እና እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ መከናወን የሚኖርባቸውን አጠቃላይ አመልካች ካርታዋችን ማዘጋጀት።

አንድ ላይ እነዚህ ሶስት ነገሮች የህዝብ ተቆማት እና አገልግሎቶችን ያካተቱ የአሌክሳንደሪያ የረዥም ጊዜ ፣ የተቀናጀ፣ ከተማ አቀፍ ረቂቅ እቅድ ይይዛሉ።

**ገፅ (ስላይድ) 5፣**

ይህ ስራ ከ2019 መጨረሻው ጊዜ  ላይ ከጀመርን ጀምሮ አጠቃላይ አቅጣጫ አመልካች ማእቀፍ ረቂቅ እና የፍላጎት ግምገማ ስራዎችን አጠናቀናል።   ይህ ቪዲዮ እስከአሁን የተማርነውን ይሳያል።

የተዘጋጀውን አጠቃላይ አመልካች ማእቀፍ  ረቂቅ እና መፍትሄዎችን በመፈለግ ጥረት በስራ ከማዋላቸውን በፊት በዚህ ወሳኝ በሆነ ሂደት ደረጃ ላይ የእርስዎን ሃሳብ አስተያየት ማየት እንፈልጋለን ።  የመጨረሻውን ተግባራት እና እቅድ በስራ እንዲውሉ ከመደረጉ በፊት በሂደቱ ላይ ተገቢው አስተያየት ለመስጠት ሌሎች አጋጣሚዎች ይኖራሉ።

**ገፅ (ስላይድ) 6፣**

በፌብሩዋሪ 2020 ከእኛ ጋር ለነበራችሁ ሰዎች ምስጋናችንን እናቀርባለን በቲ.ሲ.ዊሊያም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ። ለጉብኝት ክፍት ነው (ኦፐን ሐውስ) ፕሮግራሙ የተዘጋጀው ይህን ጥረት ለኮሚዩኒቲው ለማስተዋወቅ እና ስለአሌክሳንደሪያ የህዝብ ተቆማት ያለዎት እይታ ለመረዳት ነው።  ስለሂደቱ ፣ ስለእኛ የስራ መርህ፣ ለአሌክሳንደሪያ ኮሚዩኒቲ እርስዎ ያለዎት ፍላጎት በተመለከተ ከ250 በላይ የኮሚዩኒቲ አስተያየቶችን ተቀብለናል።

የቀረቡት አስተያየቶች የተለያዪ ርእሶችን ይመለከታል - ከከተማው አጠቃላይ የህዝብ ቦታ አጠቃቀም ጀምሮ የተመረጡ ፕሮጀክቶችን እና እድሎችን በስራ ማዋልን ይጨመራል። የተጠናቀረ የተሰባሰበ አስተያየት በድረገፅ ላይ ያገኙታል።

ከተሰባሰባው አስተያየቶች መካከል በዋነኛነት የሚታዪ ጥቂት ሃሳቦች አሉ።

- በመጀመሪያ ኮሚዩኒቲው ስለፕሮጀክት እቅድ ዝግጅት ግልፅ  የሆነ ሂደት ማወቅ ይፈልጋል።  እና ፕሮጀክት  በተመለከተ እንዴት እና መቼ ውሳኔ እንደሚሰጥ ግልፅነት እንዲኖር ይፈልጋሉ።
- ሁለተኛ አጠቃላይ አቅጣጫውን የሚመለከቱ መመሪያዎችን በአብዛኛው ደግፋችሆል።

የእርስዎ የማያቆራጥ ተሳትፎ መኖር አስደሳች ሲሆን ይህ የእርስዎ የመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ እንኳን ደህና መጡ እንላለን! የእርስዎ አስተያየት ለእኛ በጣም ጠቃሚ ነው።

**ገፅ (ስላይድ) 7፣**

አሁን እኛ የት ነው ያለነው?

**ገፅ (ስላይድ) 8፣**

ከእኛ የኮሚዩኒቲ ስብሰባ በኋላ የወደፊት እንቅስቃሴዋችን የሚመራ አቅጣጫ አመልካች ማእቀፎችን ሃሳቦችን አዘጋጅተናል።  አቅጣጫ አመልካች መመሪያዎችን የያዘው ማእቀፍ  በቀጣዪ ደቂቃዋች መመልከት ይችላሉ።  አጠቃላይ አቅጣጫ  ሁለት ከፍተኛ ደረጃ የማስተር ፕላን እቅድ አዘገጃጀት እና የወደፊት ፕሮጀክት እቅድ ዝግጅት  ደረጃዋች ያመላከታል።  በየደረጃው ዋና ክንውኖች እና እንቅስቃሴዋችን ደረጃ የሚያመለከቱ መለኪያዋች ተለይተዋል።  በመጨረሻም የፕሮጀክት ሰራተኞች እና የከተማው መሪዎች ስራ የሚመራ መሳሪያዎች እና ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተዋል።

**ገፅ (ስላይድ) 9፣**

እንደሚገምቱት የአጠቃላይ ማእቀፉ ዝርዝር ሃሳቦችን ያካተተ መረጃ ይዞል። ቪዲዬ የማእቀፉ ዝርዝር ሃሳቦችን አያካትትም። ሆኖም ግን እኛ አጠቃላይ የአሰራር መርሆዋችን ለማስታወስ እንፈልጋለን።

**ገፅ (ስላይድ) 10፣**

እነዚህ መመሪያዋች ለአጠቃላይ ማእቀፉ መሰረት ናቸው።

የመጀመሪያውን መርህ እንደ ምሳሌ እንውሰድ። "እኛ አንድ ኮሚዬኒቲ ነን እና አንድ ፖርትፎሊዮ አለን።" የእኛ የህዝብ ተቆማት - ከቤተመፅሃፍት እና ት/ቤቶች እስከ ፓሊስ ጣቢያ እና የእሳት አደጋ - ሁሉም አንድ ወጥነት ካለው አስተሳሰብ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይኸም ማለት ፕሮጀክቶች ነጣጥለን በራሳቸው እቅድ አናዘጋጅም። ሆኖም አጠቃላይ ስእሉን ገፅታውን እናያለን ። እንደ ኮሚዩኒቲ እኛ ካላን ፍላጎት ባሻግር መመልከት አለብን እና ሁሉም ፍላጎቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለብን።

የእኛ አራተኛው መርህ "አጠቃላይ እና ወጥነት ያላቸው መፍትሄዋች ዘላቂነት ያለው አገልግሎት ይሰጣል። " እኛ የረዥም፣ የ30 ዓመት እቅድ ፕሮጀክቶችን እንደ የአጭር ጊዜ ችግር የማቃለል ስራ ከማየት ይልቅ እንደ ረዥም ጊዜ ኢንቨስትሜንት እንመለከታል። የግንባታ ወጪዋች እንዲሁም የእኛ ውሳኔዋች የስራ እና የህይወት ኡደት አብረን እንመለከታለን።

በድምሩ የእኛ መርሆዋች በህዝብ ተቆማት ፕሮጀክት ተሳታፊ የሆነ ሁሉ የከተማ አቀፍ ያለውን ጠቀሜታ እና ግብ መረዳት ያስፈልጋቸዋል።

የፍላጎት ግምገማ ሂደት ውስጥ ጠልቀን ከመግባታችን በፊት እነዚህን ፍላጎቶች ምን እየመራቸው እንደሆነ እንደሚፈጥራቸው ማወቅ ተገቢ ነው።

**ገፅ (ስላይድ) 11፣**

የህዝብ ብዛት ዋነኛው ፍላጎት ከሚመሩት ዋነኛ ጉዳዬች መካከል አንዱ ነው። ባለፉት አስረተ-ዓመታት አሌክሳንደሪያ ወደ 20,000 የሚጠጉ ኗሪዋች ተጨምረዋል እና የህዝብ ተቆማት ከህዝብ መጨመር ጋር አብሮ አላደጉም።

በቀጣዩ 20 ዓመታት በተጨማሪ 30,000 ህዝብ እድገት እንደሚኖር ይገመታል ። ይኸም ለህዝብ አገልግሎት እና ተቆማት ፍላጎት ጥያቄን የበለጠ ይጨምራል።

**ገፅ (ስላይድ) 12፣**

በህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት አሁን ያሉትንና ወደፊት የሚመጡትን የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዋች ለማስተናገድ የበለጠ መቀመጫዋች ያስፈልጉናል። አሁን ያለበት የት/ቤቶች አቅም በሰንጠረዡ በአረንጎዴው መስመር የተገለፀው አሁን ካለው የተማሪዋች ቁጥር አንፃር በሰማያዊ ቀለም የሚታየው እና ወደፊት ከሚገመተው የሚመዘገቡ ተማሪዋች ቁጥር በብርቱካን ቀለም ከሚታየው ሲታይ አነስተኛ ነው።

በቀጣዪ አስርተዓመታት በሁለተኛ ደረጃ ከ1600 በላይ መቀመጫዋችን፣ በመካከለኛ ደረጃ 1200 እና በአንደኛ ደረጃ 800 ቦታዋችን ማዘጋጀት ይኖርብናል።

የተማሪዎች ቁጥር አዲስ በሚገነቡት አካባቢዎች ላይ ሳይሆን በነባሮቹ ባሉት በሁሉም ሰፈሮች ጨምሮል። አሁን ያለውን የአቅም ማነስ ለመፍታት እንዲሁም የወደፊቱን እድገት ለማስተናገድ አሁን ያሉት ት/ቤቶችን አቅም ማሳደግ ይኖርብናል።

**ገፅ (ስላይድ) 13፣**

የህዝብ ብዛት ዋነኛው ፍላጎት ከሚመሩት ዋነኛ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። አሁን ያሉት ህንፃዎች የውስጥ መሳሪያዎቻቸው መቀየር ያለብት እድሜ ላይ ደርሰዋል።

በአማካኝ የእኛ ህንፃዎች እድሜ ከ34 ከዚያ በላይ እድሜ አላቸው። የት/ቤቶች በአማካኝ 54 ዓመት እድሜ አላቸው።

**ገፅ (ስላይድ) 14፣**

በመላው ከተማው ብዙ ፍላጎቶች አሉ።

እኛ ያሉን ህንፃዎች የእድሜ ችግር አላቸው፤ ጣራ፣ የቧንቦ እና የHVAC መሳሪያዎች በተወሰነ ጊዜ መቀየር አለባቸው።

የህንፃ ዲዛይን ከእድሜ ጋር ይያዛል። ለምሳሌ፣ የትምህርት አሰጣጥ ሞዴሎች የትምህርት ቤት ግንባታ ከ60 እና 70 ዋቹ ዓመታት በኋላ ተለውጠዋል። ቤተ-መፅሃፍት ከመፅሃፍት በተጨማሪ ሌሎች ነገሮች ያቀርባሉ። የእሳት አደጋ መከላከያዎች ትላልቅ መኪናዎች ማስተናገድ ይኖርባቸዋል። ስለሆነም ህንፃዎቹ በአግባቡ መስራት እንዲችሉ ዘመናዊ መደረግ ይኖርባቸዋል።

የህዝብ ብዛት እና የተማሪዎች ቁጥር መጨመር በእኛ ፍላጎት ላይ በቀጥታ ተፅእኖ ያሳድራል። አሌክሳንደሪያ እያደገ ሲመጣ ሁሉንም ኗሪዎች አግባብነት ያለው አገልግሎት መስጠት እና የእነዚያ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ማሟላት ይኖርበታል። አሁን ያለውን እና አዲስ አገልግሎቶች ለሁሉም የአሌክሳንደሪያ ኗሪዎች የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት አለባቸው።

በመጨረሻም የከተማውን ስትራቴጂክ አላማዎች የሚያንፀባርቅ ፍላጎቶች እና የተነቃቃ ህይወት ያለው ከተማ ሆኖ እንዲቀጥል ያግዛል።

ቀጣዩ ስላይድ የፍላጎቶችን አጠቃላይ እይታ ያሳያል፤ የቀረቡበት እኛ "የአካዳሚ አቀራረብ ዘዴ" በምንለው መንገድ ነው - እነዚህ ፕሮጀክቶች በአሁኑ ወቅት ገንዘብ የተመደበላቸው የቆሚ ንብረት(ካፒታል) ማሻሻያ ፕሮግራም አይደሉም። እንዲያውም የአሌክሳንደሪያ ፍላጎት እንደመሰረት መነሻ የሚያሳዩ አሁን ባለን እውቀት ግንዛቤ ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

**ገፅ (ስላይድ) 15፣**

በአሌክሳንደሪያ በርካታ አስቸኳይ ፍላጎቶች አሉ። አስቸኳይ ፍላጎቶች በቀጣይ 10 ዓመታት ወይም በዚያን ያህል ግዜ መፍትሄ ማግኘት የሚገባቸው ጉዳዩች ናቸው በሁኔታዎች እና በቀጥታ በሚያስፈልግ አገልግሎት እንደ ትምህርት ቤት የአቅም ፍላጎት ጥያቄዎች ምላሺ በመስጠት ። በመላው ከተማው ተበታትነው ነው ያሉት። አብዛኛዎቹ የጥገና ፍላጎቶች ለሌላ ግዜ እንዲካሄዱ ወይም ለዓመታት

ሳይከናወኑ እንዲዘገዩ ተደርጎል።

9 ት/ቤቶች የገንዘብ ወጭ ይጠይቃሉ እና በድምሩ 3600 መቀመጫዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል ተጨማሪ የተማሪዎችን ቁጥር ለማስተናገድ።

በመጀመሪያ በአደጋ ጊዜ ምላሹ ለሚሰጡ አዲስ ተቆማት ያስፈልጋቸዋል ፤ 5 አዲስ የእሳት አደጋ ጣቢያዎች እና ለፓሊሶችና ለእሳት አደጋ ባለሞያዎች ስልጠና መስጫ ተቆማት። ብዙዎቹ የአሌክሳንደሪያ የእሳት አደጋ ጣቢያዎች ዘመናዊ የእሳት አደጋ ከባድ መኪናዎቹን እና መሳሪያዎችን መያዝ አይችሉም። ከ5 ጣቢያዎች 4 አዲስ ቦታዎች ያስፈልጋቸዋል በከተማው ውስጥ ተገቢውን ምላሺ ለመስጠት።

**ገፅ (ስላይድ) 16፣**

የአሌክሳንደሪያ የመካከለኛ ጊዜ ፍላጎቶች የተለያዩ እና ሰፊ ናቸው። ህንፃዋቹ እያረጁ ሲሄዱ በቀጣዩቹ 15 እስከ 20 ዓመታት ጉዳዩ መመልከት ይኖርብናል እንዱሁም አዲስ ተጨማሪ አቅም መጨመር ይኖርብናል።

ይህ ፍላጎት አዲስ መረጃ እንደተገኘ በየጊዜው ሊቀያየር ይችላል። ለምሳሌ የአዲስ ት/ቤት ተመዝጋቢዋች ግምት ማደግ ወይም የ2020 የህዝብ ቆጠራ ውጤት። ከእኛ አጠቃላይ መርሆች ጋር በሚጣጣም መልኩ የእኛ ህንፃዋች ተለዋዋጭ በሚሆን መልኩ ዲዛይን ማዘጋጀት ይኖርብናል እና ለለውጥ የሚመች መሆን ይኖርባቸዋል።

**ገፅ (ስላይድ) 17፣**

የረዥም ጊዜ ፍላጎት የሚያተኩረው የእኛን ሃብቶች በጥሩ የመጠበቅ እና አሁን በምናዘጋጀው ግምት መሰረት ላሉን ፍላጎቶችን ምላሺ መስጠት ይኖርብናል። በርካታ ፍላጎቶቻችን ህንፃዋች ናቸው በቅርብ ጊዜ ያሻሻልናቸው ወይም የገነባናቸው እና የ30-40 ዓመት እድሜ ላይ ሲደርሱ ትላልቅ ወጪዎችን ሊጠይቁ ይችላሉ። ከእኛ አጠቃላይ መርሆች ጋር በሚጣጣም መልኩ የእኛ ህንፃዋች ተለዋዋጭ በሚሆን መልኩ ዲዛይን ማዘጋጀት ይኖርብናል እና ለለውጥ የሚመች መሆን ይኖርባቸዋል።

**ገፅ (ስላይድ) 18፣**

በአጠቃላይ የፍላጎት ግምገማ ማድረግ የረዥም ጊዜ አመለካከት ምን ያህል ወጪ እንደሚያስፈልግ ለመረዳት ያስችላል።

- በአስቸኳይ፣ በመካከለኛ እና በረዥም ጊዜ ፍላጎቶችን በማየት በቅርብ ጊዜ ኢንቨስትሜንት ወጭ ቢደረግም አሁንም ቢሆን በርካታ ፍላጎቶችን በቀጣይ ማሟላት እንደሚኖርብን እንረዳለን።
- እናም እነዚህን ፍላጎቶች በሙሉ ለማሟላት በቂ የገንዘብ ሃይል የለም።
- እንዲሁም ያለውን ፍላጎት በከተማው በሙሉ የተሰራጨ እንደሆነ ይታያል - በየኮሚዪኒቲው ላይ ያለውን ተፅእኖ እና በአንድ ላይ መስራት እንደሚኖርብን ያሳያል።
- በመጨረሻም ህንፃዋች በዘላቂነት እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ይታወቃል እና በርካታ የጥገና ስራዋች ወደፊት እንዲካሄዱ ጊዜው እንዲራዘም የተደረገ አሉ። የህዝብ ንብረቶችን ለመጠበቅ እና ለማደስ እቅዱ በጣም አስፈላጊ ነው።

እነዚህን ፍላጎቶች ስንመለከት በጥቅሉ ዋናውን ትልቁን እይታ እንድንመለከት ስለሆነም ያሉን ችግሮች በግዜ ለማቃለል እንድንችል ፈጣሪ ለመሆን እድሎችን እናገኛለን።

ስለፍላጎት ግምገማ ዝርዝር መረጃዎች  በድረገፁ ላይ ይገኛል።

**ገፅ (ስላይድ) 19፣**

አሁን የማእቀፉን አካል እና የፍላጎት ግምገማ ተመልክተዋል በዚህ ሂደት ቀጣዩ ሂደት ምንድን ነው?

**ገፅ (ስላይድ) 20፣**

ለመጪው 30 ዓመታት መንገድ የሚያሳይ አቅጣጫ አመልካች ካርታ ለማዘጋጀት ዝግጁ ሆነናል።  ሆኖም ግን ስለስትራቴጂዎች እና መፍትሄ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነገሮች ከማውራታቸን በፊት  ማእቀፉን ስለሚመሩ እና መነሻ የሚሆኑ የፍላጎቶች ግምገማ  ዛሬ እዚህ ያዩትን ጉዳዮችን ለማሻሻል እና የመጨረሻ መልክ ለማስያዝ የእርስዎን አስተያየት ማግኘት እንፈልጋለን።

**ገፅ (ስላይድ) 21፣**

ለእኛ ሰፊ ፍላጎት ሊውሉ የሚችሉ በርካታ ስትራቴጂዎች አሉ።  ውጤታማ ለመሆን ፈጣሪ መሆን እንዳለብን እናውቃለን።

መሬት የማይገኝ ሃብት እንደሆነ ስለምንረዳ አሁን ያሉንን የመሬት ሃብት(ሪይል ስቴት) በአግባቡ መጠቀም አለብን።  ይህም ማለት አንድን ቦታ መልሶ መገንባት ሲያስፈልግ እንዴት ህፃውን መገንባት እና ቦታው ዲዛይን መዘጋጀት እንደሚኖርበት እና ቦታውን ከሌሎች የህዝብ አገልግሎት መስጫ ጋር መጋራት እንዳለባቸው የሚኖሩ እድሎችን ማሰብ ያስፈልጋል።

አሌክሳንደሪያ ይህን ሁኔታ ያጋጠመው ብቸኛ ቦታ አይደለም። አንድ ተቆማ ለማዘጋጀት እድል ሊኖር ይችላል ከሌሎች የአስተዳደር አካላት ጋር በፌርፋክስ ወይም ከአርሊንግተን ካውንቲ - እና የግንባታ እና የስራ ማስኬጃ በጀት በጋራ ለመጋራት ሁኔታው ሊፈቅድልን ይችላል።

ከብዙ ስትራቴጂዎች መካከል ልንመለከለታቸው የሚችሉ 6 ምሳሌዎች አሉ ። አዲስ ጠቃሚ የሆኑ ስትራቴጂዎችን ለመመልከት  የእርስዎ ሃሳብ እንደ ግብዓት እንዲያገለግል እንፈልጋለን።

**ገፅ (ስላይድ) 22፣**

ስለሆነም እባክዎን  ሃሳብዎን ለማካፈል ጥቂት ግዜ ይውሰዱ።  በከተማው ያለ ፍላጎት ያልታዩ ካሉ ለመረዳት ለማስታወስ  እንድንችል የእርስዎን አስተያየት እንፈልጋለን። እነዚህን ፍላጎቶች በፈጠራ መንገድ ለሚማላት የሚኖሩ ሃሳቦችን ማግኘት እንፈልጋለን።

**ገፅ (ስላይድ) 23፣**

እባክዎን መጠየቁን ይሙሉ እና በሂደቱ የእርስዎን ሃሳብ ያካፍሉ።

መጠየቁን በሚከተለው መንገድ ማግኘት ይቻላሉ፤

- በመረጃ መፈለጊያው (ብራውዘር) ላይ ይህን ድረገፅ(ዌብሳይት) አድራሻ በመፃፍ፤ **bit.ly/AlexandriaJFMP**
- ቪዲዩ በተጫነበት ድረገፅ ላይ የጋራ ተቆም ማስተር ፕላን  መመልከት ይቻላል።

ይህን ቪዲዩ ለሌሎች እንዲመለከቱ፤ ለጎረቤትዎ፣ የኮሚዩኒቲ ድርጅቶችን እና ጎደኞች ማስተላፍ ይቻላሉ ስለሆነም አሌክሳንደሪያ ሁሉም ኗሪዋች ድምፃቸው እንዲሰማ ያግዛሉ።